# የዜጎች መድረክ

ኢዜማ

ቅፅ 2 ቁጥር 74 ጥር 27 ቀን 2013ዓ.ም

በኢዜማ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ

## ‹‹ኢትዮጵያ ጥሩ ዕድል አላት››

ኃይለመስቀል በሸዋምየለህ



# ቆይታ

## < <ኢትዮጵያ ጥሩ ዕድል አላት> >

### ኃይለመስቀል በሸዋምየለህ

ኃይለመስቀል በሸዋምየለህ በህትመት ሚዲያው የራሱን አሻራ ያሳረፈ ጋዜጠኛ፣ ፀሀፊ እና ተርጓሚ ነው፡፡ በፍትህ እና በልዕልና ጋዜጣዎች እንዲሁም በአዲስ ታይምስ እና በፋክት መፅሄቶች ይፅፋቸው በነበሩት ትንታኔያዊ ሀቲቶቹ ብዙዎች ያስታውሱታል፡፡ ከሙያ አጋሩ ሙሉነህ አያሌው ጋር በመሆን «የመለስ ውርሶች» በሚል ርዕስ አንድ መፅሐፍ አሳትሟል፡፡ ከሌሎች የሙያ አጋሮቹ እስክንድር ነጋ፣ ተመስገን ደሳለኝ፣ ዳዊት ታደሰ እና ሙሉነህ አያሌው ጋር በጋራ በመሆን «የሕዳሴው አብዮት» የተሰኘ መፅሐፍ ለንባብ አብቅቷል፡፡ በግሉ ደግሞ «የኃይለማሪያም ዕዳ እና የሙስሊሙ ትግል» የተሰኘ መፅሐፍ ፅፏል፡፡ በቅርቡ ደግሞ በአፍሪካ ቀንድ ዙሪያ የሚያጠነጥነውን የዕውቁ የፖለቲካ ሳይንቲስት ክርስቶፈር ክላፋም “The Horn Of Africa፡ State Formation and Decay” የተሰኘውን ወደ አማርኛ የመለሰው መፅሐፍ በቅርቡ ገበያ ላይ ይውላል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ ኃይለመስቀል በሸዋምየለህ የዚህ ሳምንት የዜጎች መድረክ የ«ቆይታ» አምድ እንግዳ ነው፡፡ ከእሱ ጋር ያደረግነውን ተከታዩን ቆይታ እንድታነቡት እንጋብዛለን፡፡



*ከእኛ ጋር ቆይታ ለማድረግ ፍቃደኛ ስለሆንክ፤ በአንባቢዎቹ ስም ምስጋናዬን ላቀርብልህ እወዳለሁ፡፡*

እኔም አመሰግናለሁ፡፡

*ከህትመት ሚዲያው ገለል ብለህ መቆየትህን ተከትሎ፣ ኃይለመስቀል ጠፍቷል የሚሉ አሉ፡፡ ጠፍተሀል ልበል?*

ብዙ አልጠፋሁም፡፡ ከሰሞኑ አንድ ዩቲዩብ ላይ ፅሁፎቼን እያቀረብኩ ነው፡፡ በተጨማሪም በሳምንት አንድ ጊዜ በሰሞናዊ ጉዳዮች ላይ እየለፈለፍኩ ነው፡፡

*የድህረ-ሕወሓቷ ኢትዮጵያ ዕጣ ፈንታ ምን የሚሆን ይመስልሀል?*

መልካም ጎኖች አሉት፡፡ አንዱ መልካም ጎን፣ ዴሞክራሲያዊ ሽግግሮችን ለማድረግ አንድ ጨቋኝ እና ጠቅላይ የብሔርተኛ ስብስብ አለመኖሩ አንዱን የዴሞክራሲያዊ ሽግግር ዕግዳት አንስቷል፡፡ ይመለስ አይመለስ ባናውቅም ቅሉ፤ በጣም ተቋማዊነት የነበረው የብሄር ተኮር የጥቅመኝነት ሥርዓት ቢያንስ ለጊዜው ከሕወሓት ጋር ተወግዷል፡፡ ከዚህ አኳያ ኢትዮጵያ ጥሩ ዕድል አላት፡፡ ያንን የመጠቀም እና ያለመጠቀም ጉዳይ፣ አሁን ሥልጣን የያዘው ልሂቅ ስብስብ፣ የተቃውሞ ፓርቲዎች፣ ሲቪል ማኅበረሰብ፣ የምሁራን እና የጋዜጠኞች ሚና ነው፡፡

*የሕወሓት መደምሰስ ከኢትዮጵያ አልፎ ለአፍሪካ ቀንድ ሰላም የሚያመጣ ነው የሚሉ ወገኖች አሉ፡፡ የአፍሪካ ቀንድ ፖለቲካን በአንክሮ እንደሚከታተል አንድ ፀሀፊ፣ በዚህ ላይ ምን ሀሳብ አለህ?*

ይሄ ትክክል ነው፡፡ አንድ ቀላል ማሳያ ልጥቀስ፡፡ ሳልቫኪር ከወራት በፊት እንደተናገረው፣ በእሱና በተቀናቃኙ ሪክ ማቻር መሀል ሽምግልና የተቀመጠው የሕወሓት ሰው ከመሸምገል ይልቅ ሲያጣላን ነበር ማለቱ አነስተኛም ቢሆን የሕወሓትን አሉታዊ ሚና ይነግረናል፡፡ ቀንዱ ላይ ሰላም የሚያመጣው ዋናው ጭብጥ፣ የምዕራብውያንን ተላላኪ የነበረው ሕወሓት ሱማሊያ ውስጥ የፈጠረው ውጥንቅጥ ነው፡፡ መጠቀስ የሚችለው ሌላው ነገር ኤርትራ ላይ ከኢጋድ እስከ የተባባሩት መንግሥታት ድረስ በመሄድ በከፍተኛ ማዕቀብ ያቺ አገር እንድትዳከም የሄደበት የከፋት ልክ ነው፡፡ ከኤርትራ ጋር በማይረባ ወይም አንዳንዶች እንደሚሉት ሁለት መላጦች በማበጠሪያ ተጣሉ ያሰባለ፣ ከመቶሺህ የማያንሱ ልጆች ያስጨረሰውን ረብ የለሽ ጦርነት አንስተን ማለፍ እንችላለን፡፡ በዋናነት የቀንዱ አገራት ሊያስተባብራቸው የሚችል ስትራቴጂያዊ፣ ባህላዊ እና በዋናነት ደግሞ ኢኮኖሚያዊ በቂ ምክነያት ኖሯቸው ሳለ፤ ይሄ እንዳይሆንና ድርጅቱ ብቻውን የበላይነት እንዲኖረው ያደረገው ነገር ሲታይ፣ የድርጅቱ መወገድ ለቀንዱ አገራት ጭምር ትልቅ በረከት ነው፡፡

*ዐቢይ አህመድ፣ ሕወሓትን መደምሰሱና ኢሕአዴግን ማፍረሱን ተከትሎ ከምርጫው በኋላ አምባገነን ሆኖ የመውጣት እድሉ የሰፋ ነው የሚሉ የፖለቲካ ተንታኞች አሉ፡፡ በዚህ ላይ ያለህ ዕይታ ምን ይመስላል?*

እስከሆነ ልክ ጥርጣሬውን እጋራለሁ፡፡ የኢትዮጵያ ሥርዓተ-መንግሥት የፖለቲካ ባህል ለአንድ ሰው የብቻ አገዛዝ የተመቸ መሆኑ ይታወቃል፡፡ የዐቢይ ከሕወሓት ጋር የነበረውን ግጭት በብረት እንዲፈታ ነገሮች ማስገደዳቸው ሰውየውን ሊያደነድኑት ይችላሉ ብሎ መጠርጠር ሊያስኬድ ይችላል፡፡

ስለቅቡልነት ሶስት መስመሮች አሉ፡፡ ሕዝባዊ፣ ሕጋዊ እና በምርጫ የሚመጣ ቅቡልነት ይባላሉ፡፡ ዐቢይ የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ አሉት፡፡ አሁን የሚቀረው ሶስተኛው ነው፡፡ ይህኛውን ቅቡልነት በተወሰነ ደረጃ በፍትሀዊ ምርጫ የሚያገኘው ከሆነ፣ አምባገነን የመሆን ውስጣዊም ሆነ ውጫዊ ግፊቶቹን ሊገታቸው ይችላል፡፡ ጥርጣሬው እውን ቢሆን፤ አንድም ከሰባተኛው ብሔራዊ ምርጫ በፊት የሚሆን አይመስለኝም፡፡ ከመናፍቃኑ ጋር የማልስማማው አንድ ነገር፤ ልክ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን ሞክረን ተመልሰን እዚህ ውስጥ የተገኘን ይመስል፣ ኢትዮጵያ ከዚህ በኋላ አምባገነንነትን አትሸከምም የምትለውን ጨዋታ ብቻ ነው፡፡ ቢገጥመን እንኳ ጠቅሰን ማለፍ የሚያስፈልገን፤ ይሄንን የሚጠራጠሩ ሰዎች ስለ ደግ (benevolent) አምባገነን እያነበቡ እንዲቆዩ ነው፡፡ ሰውዬው ወደዚያ ከተሻገረ እንኳን ሊሆን የሚችል የሚችለው ያንን ነውና፡፡

*ዐቢይ ከሕወሓት ጋር የነበረውን ግጭት በብረት መፍታቱን ተከትሎ ከሱዳን ጋር ያለውን የድንበር ውዝግብም በዛው መንገድ መፍታት አለበት የሚሉ አሉ፡፡ ትስማማለህ?*

አልስማማም፡፡ አንዱ የማልስማማበት ምክነያት አሁን ከጠየከኝ፤ ዐቢይ አምባገነን ሊሆን ይችላል ከሚለው ጋር በቀጭን ክር ይተሳሰራል፡፡ ምን ለማለት ፈልጌ ነው? መንግሥቱ ኃይለማሪያም ከሱማሊያ ወረራ በኋላ፤ መለስ ዜናዊ ደግሞ ከባድመ ተኮር ጦርነት ማግስት ወደ ሙሉ በኩለሄ አምባገነንነት ለመሻገር ወራትን አልጠበቁም፡፡ ጦርነቱ ቢቀሰቀስ ኢትዮጵያ ታሸንፋለች የሚለውን ቅደመ ግምት ከያዝን፤ እንደ መንግሥቱ ኃይለማርያም 1971፤ እንደ መለስ 1993 ሁሉ፤ ይሄም የዐቢይ 2013 ሊሆን ይችል ይሆናል፡፡

በዚህ ሶስት ዓመታት ውስጥ ሰውዬው ከውስጥም ከውጪም የተጋፈጣቸው ተግዳሮቶች ላይ ይሄንን ጦርነት ከጨመርንበት፤ በድሉ ማግስት ኮሎኔል ዐቢይ አህመድን ለመጠበቅ መዘጋጀት ይኖርብናል፡፡ እኔ እንደታዘብኩት ውረድ እንውረድ እያሉ ያሉት፤ በብአዴን ቀጭን መስመር የተንጠላጠሉ አካባቢያዊ ፖለቲከኞችና የፖለቲካ ፍላጎት ያላቸው ባለሀብቶች ናቸው፡፡

*የፖለቲካ ፓርቲዎች ምርጫ 2013 ተከትሎ እያደረጉት ያሉ የምርጫ ዝግጅቶች እንዴት ትመለከታቸዋለህ?*

ምንም ዝግጅት ስለመኖሩ አልሰማሁም፤ አላየሁም፡፡ ምናልባትም ግን ምርጫ 1997ን እንደ መነሻ ከወሰድነው፤ በቀጣይ ወር አደባባዩ ጭቅጭቅ ይበዛበት ይሆናል፡፡

*ኢዜማ ለምርጫ ዝግጅት መጀመሩ ይታወቃል፡፡ የእሱን ዝግጅት እንደ ዝግጅት አትቆጥረውም?*

አስተያየቴ ከ50 በላይ ስለሚሆኑት ፓርቲዎች ጥቅል ምልከታ እንጂ ስለ ኢዜማ አይደለም፡፡

*ይሁን፤ የኢዜማን ምርጫ ዝግጅትስ እንዴት ትገመግመዋለህ?*

ምንም ጥርጥር በሌለው መንገድ ኢዜማ ከሌሎቹ ፓርቲዎች በተሻለ እየተዘጋጀ እንደሆነ፤ የሰሞነኛው የፓርቲው የምርጫ ዕጩዎች የአመራረጥ ሂደት እና ዕጩዎችን እያቀረበ እንደነበር መመልከታችን የተሻለ ዝግጅት እንዳለው ያሳያል፡፡ ያም ሆኖ ግን አራት ወራት ለቀረው ምርጫ ማኒፌስቶውን ለማቅረብ መዘግየቱን ሳንነቅፍ ግን አናልፍም፡፡

*ኢዜማ ለምርጫው እያደረገ ካለው ዝግጅት አንፃር፣ ምርጫው ላይ ምን ውጤት የሚያስመዘግብ ይመስልሃል?*

ይሄንንእናቀጣዩን7ኛውአገርአቀፍ ምርጫ ከብልፅግና ጋር ወደፊት (ከሸሙጣዊ ስላቅ ጋር) ማለታችንን እርግጠኛ ከመሆን በተጨማሪ፤ ኢዜማን አስመልክቶ ግን፣ ልል የምችለው ነገር ኢ-ወጋዊውን የፖለቲካ ትሬንድ ተከትዬ ደህና ግምት ልስጥ ብል፤ ኢዜማ አዲስ አበባን በቀጣይ የሚያስተዳድር ይመስለኛል፡፡ ከዚያ ባለፈ አማራ ክልል ላይ በጣም ጥቂት የክልል ምክር ቤት ወንበር፤ አነስ ያለ ደግሞ የፌደራል ወንበር፤ ወዲያ ወደ ደቡብ ደግሞ አርባምንጭ እና ጉራጌ ዞን ግድም ጥቂት ወንበሮችን ከአልፎ አልፎ የኦሮሚያ አካባቢዎች ወንበሮች ጋር የሚያገኝ ይመስለኛል፡፡


## አድራሻ

ስልክ
+251118592950

ኢሜይል
ethzema@gmail.com

ትዊተር
www.twitter.com/ethzema

ፌስቡክ
www.facebook.com/ethzema

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ)

ጥር 27 ቀን 2013 ዓ.ም
አዲስ አበባ

*የኢዜማን ፕሮግራም እንዴት አገኘኸው? ምንስ ክፍተት አስተዋልክበት?*

አንድ ካናደደኝ፤ አንድ ደግሞ ድርጅቱ ከተሸኮረመመበት ልጀምርልህ:: ኢትዮጵያ ወደብ አልባ ስለሆነች የባህር በር ያስፈልጋታል፤ ይህን ደግሞ በሕጋዊ እና በሰላማዊ መንገድ እናስፈፅማለን ይላል:: መቼም የባህር በር ሲሉ በርበራን አይደለም:: እየተነገረን ያለው ስለ አሰብ ነው:: ይህን አመለካከት «የያዕቆብ ሲንድረም» ብለን እናፊዝበትና እንቀጥል:: አሰብን ከኤርትራ ነጥሎ ከጉልበት ውጪ ሰላማዊ በለው፤ ሕጋዊ በለው፤ ታሪካዊ በለው፤ ኢኮኖሚያዊ አንድም ወደ ኢትዮጵያ የማዋሃጃ ምንም መንገድ የለም:: ኤርትራን በቀይ ባህር እና በአሰብ መነፅር በኩል ማየት መቼ እንደምናቆም ብቻ ነው የሚገርመኝ::

‹

አሁን በኢትዮጵያ እና በኤርትራ የተደረገው ስምምነት አንደኛው አንቀፅ፣ ሁለቱም የሌላኛውን አገር ሉዓላዊነት እንደሚቀበሉ ይደነግጋል:: በተያያዥም የአልጀርስ ስምምነትን ካለ ቅድመ ሁኔታ ኢትዮጵያ እንደምትቀበል ስምምነቱ ይጠቅሳል:: ይሄ ማለት አሰብ የኤርትራ አካለ- ክፍል መሆኗን መስማማት መቀበል መሆኑን ለፕሮግራም አርቃቂዎቹ ማስታወስ አያስፈልገንም:: ሲመስለኝ የፓርቲው ልሂቃን ይሄ ጠፍቷቸው አልያም የያዕቆብን ሲንድረም ተጋርተው ነው ለማለት ይከብደኛል:: ይልቅ ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ የሚለው የፓርቲው የአሁኑ እና የወደፊት ማኅበራዊ መሰረቱ፤ ይሄንን እንዲሉ በማስገደዱ ያደረጉት አሁናዊ ፖለቲካዊ ትክክለኝነት ይመስለኛል::

ፓርቲው የተሸኮረመመበት ሌላኛው አንቀፅ ስለ ቋንቋ የሚናገርበት ክፍል ነው:: ፕሬዝዳንታዊ ሥርዓት ለዘውግ ተኮሩ ማኅበራዊ መበጣጠስ በመፍትሄነት ይጠቅማል ብሎ የሚያምን ፓርቲ (ትክክልም ነው) ብሔራዊ ቋንቋ ያስፈልገናል ለማለት ምን እንዳስቸገረው ግራ ይገባል:: ተያያዡ ፖለቲካዊ መሸኮርመም፤ ከአማርኛ ውጪ ተጨማሪ ቋንቋዎች ሲባል መቼም ስለ ኦሮምኛ እንጂ ስለ አገውኛ እስካልሆነ ድረስ፤ ኦሮምኛ ሁለተኛው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቋንቋ የሚል ሀሳብ ፕሮግራሙ ውስጥ ቢኖር እንዴት በበጀ:: በተለይም ኢዜማን በአሀዳዊነት ለሚያሙ ብሔርተኞች አንድ ጥሩ ምስ ይሆን ነበር::

ሌላው ሳልጠቅስልህ ማለፍ የማልፈልገው ስለ ሕገ-መንግሥት የተነሳውን የፕሮግራሙ ክፍል ነው:: በሕዝበ-ውሳኔ ሕገ-መንግሥቱ እንዲሻሻል እንደሚፈልግ ቢጠቅስም፣ ኋላ የምርጫ ማኒፌስቶ ላይ ▶

‹‹አሁን በኢትዮጵያ እና በኤርትራ የተደረገው ስምምነት አንደኛው አንቀፅ፣ ሁለቱም የሌላኛውን አገር ሉዓላዊነት እንደሚቀበሉ ይደነግጋል:: በተያያዥም የአልጀርስ ስምምነትን ካለ ቅድመ ሁኔታ ኢትዮጵያ እንደምትቀበል ስምምነቱ ይጠቅሳል:: ይሄ ማለት አሰብ የኤርትራ አካለ- ክፍል መሆኗን መስማማት መቀበል መሆኑን ለፕሮግራም አርቃቂዎቹ ማስታወስ አያስፈልገንም:: ሲመስለኝ የፓርቲው ልሂቃን ይሄ ጠፍቷቸው አልያም የያዕቆብን ሲንድረም ተጋርተው ነው ለማለት ይከብደኛል:: ይልቅ ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ የሚለው የፓርቲው የአሁኑ እና የወደፊት ማኅበራዊ መሰረቱ፤ ይሄንን እንዲሉ በማስገደዱ ያደረጉት አሁናዊ ፖለቲካዊ ትክክለኝነት ይመስለኛል::

ፓርቲው የተሸኮረመመበት ሌላኛው አንቀፅ ስለ ቋንቋ የሚናገርበት ክፍል ነው:: ፕሬዝዳንታዊ ሥርዓት ለዘውግ ተኮሩ ማኅበራዊ መበጣጠስ በመፍትሄነት ይጠቅማል ብሎ የሚያምን ፓርቲ (ትክክልም ነው) ብሔራዊ ቋንቋ ያስፈልገናል ለማለት ምን እንዳስቸገረው ግራ ይገባል:: ተያያዡ ፖለቲካዊ መሸኮርመም፤ ከአማርኛ ውጪ ተጨማሪ ቋንቋዎች ሲባል መቼም ስለ ኦሮምኛ እንጂ ስለ አገውኛ እስካልሆነ ድረስ፤ ኦሮምኛ ሁለተኛው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቋንቋ የሚል ሀሳብ ፕሮግራሙ ውስጥ ቢኖር እንዴት በበጀ:: በተለይም ኢዜማን በአሀዳዊነት ለሚያሙ ብሔርተኞች አንድ ጥሩ ምስ ይሆን ነበር:: ››





እንደሚያነሳቸው ባምንም፣ በፕሮግራም ደረጃ የሚሻሻሉ አንቀፆችን መጥቀስ የተሻለ ይሆን ነበር ብዬ አስባለሁ:: (ምክንያቱም በእርግጠኝነት እነግርሀለው፤ ምርጫው ሲቃረብ የትኞቹ አንቀፆች እንዲቀየሩ ትፈልጋላቹህ? ተብሎ የፓርቲው ሰዎች ሲጠየቁ አንዱ ከአንዱ የተለያዩ አንቀፆችን መጥቀሱ አይቀሬ ነው) በራሱ በሕገ መንግሥቱ መንገድ ፓርቲው ይቀየራሉ ብሎ የሚያስባቸውን አንቀፆች እንደማይቀየሩ መቀበሉን አደንቃለሁ:: ምክንያቱም ፓርቲው ከሚከተለው የዜግነት ፖለቲካ አኳያ እንደ የመሬት ስሪት እና የፌደራሉ አወቃቀርን የመቀየር ውሳኔው፣ ከዚህ ሕገ-መንግሥት ላይ ከእነዚህ ከሁለቱ አንዱን አንቀፅ ብታነሳ ሙሉው ሕገ-መንግሥቱ መናዱን መረዳታቸውን ትመለከታለህ:: ፓርቲው የትኛው የምርጫ ሥርዓት የተሻለ ነው ብሎ እንደሚያምን አለመጥቀሱንም፣ እንደ ክፍተት ጠቅሰነው ብናልፍ አይጎዳም::

*ፕሬዝዳንታዊ ሥርዓትን መከተልን ምርጫው ማድረጉንስ እንዴት ትመለከተዋለህ?*

የፕሬዝዳንታዊ ሥርዓት አገሪቷ ካለችበት ውጥንቅጥ ሊያወጣት ከሚችሉት ሥርዓታዊ አደረጃጀቶች አንዱ እና ጠቃሚ መሆኑን እስማማለሁ:: ግን ደግሞ ፓርላሜንታዊ ሥርዓትን መቼ ሞክረነው ነው?! አይጠቅምም ብለን የምንከራከረው የሚል ጥያቄ ማንሳት ተገቢ ነው::

*ኢዜማ ማኅበራዊ ፍትህን አሰፍናለው በማለቱ ለተወሰነ የማኅበረሰብ ክፍል የቆመ እንጂ ለግለሰብ ቅድሚያ የሚሰጥ አይደለም የሚሉ አሉ:: ይህን አስተያየት እንዴት ትመለከተዋለህ?*

የማኅበራዊ ፍትህ ዋና መሰረት ግለሰብ ነው:: ይህን ለሚሉ ሰዎች ስለ ማኅበራዊ ፍትህ አንድ ብያኔ እንስጥ:: ማኅበራዊ ፍትህ ማለት በግለሰብ እና በማኅበረሰብ መካከል የሚኖርን የግዴታዎችን እና የመብቶች ተቃርኖ ለማለዘብ የሚበጅ የሚገነባ ማኅበራዊ ውል ነው:: በማኅበረሰብ እና በመንግሥት መሀል የሚኖረውን ማኅበራዊ ውል በማኅበራዊ ፍትህ ኃልዮት በኩል ስትመለከተው፣ ቅጥ ያጣ ከፍተኛ የኢኮኖሚ መደብም ሆነ የሚዘገንን ድህነት እንዳይኖር ያንን ማረቂያ ሥርዓት ነው:: ለመደናገሩ የሚመስለኝ ሌላይኛው ምክንያት፣ ሶሻል ጀስቲስ የሚለውን ኀልዮት ወደ አማርኛ ማኅበራዊ ፍትህ ብለን መተርጎማችን ያመጣው የቋንቋው ድክመት ነው:: ኀልዮቱ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ መገፋቶችን ለመፍታት በማርክሲዝም እና በኒኦ-ሊበራሊዝም መካከል እንደቆመ ርዕዮት ሆነ ሳለ፣ የአማርኛው ፍቺ ጤና እና ትምህርት መሰል ጉዳዮች ላይ ብቻ የተንጠለጠለ ፋካሬያዊ ትርጉም ብቻ መስጠቱ አንዱ ምክንያት ይመስለኛል::

የኢትዮጵያ አጠቃላይ እድገት አንዱ ማነቆ በማዕከል እና በዳርቻዎቹ ባሉት ማኅበረሰቦች መሀከል ያለው ሁሉን አቀፍ (ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ) ዝንፈት መሆኑን የሚቀበል ማንም ሰው፣ ከራሷ ጋር የታረቀች አገር ለመገንባት ይሄንን በአንዳች አዲስ ማኅበራዊ ውል መፍታት እንዳለበት ይቀበላል:: ለዚህ ደግሞ ከማኅበራዊ ፍትህ የተሻለ አዲስ ማኅበራዊ ውል መገንቢያ መኖሩን እጠራጠራለሁ:: ይሄንን ማኅበራዊ ውል የሚተገብሩ የስካንዲኒቪያን አገራት በዓለም አቀፉ የሀፒነስ ኢንዴክስ ከአሜሪካ እና ከምዕራብ አውሮፓ የተሻለ ደረጃ ላይ መሆናቸውን ስትመለከት፤ መቼም ደስታ የሚለካው የግለሰብ እንጂ የቡድን አይደለምና በሁለቱ መካከል ተቃርኖ እንደሌለ ማስታወሻ

የማኅበራዊ ፍትህ ዋና መሰረት ግለሰብ ነው:: ይህን ለሚሉ ሰዎች ስለ ማኅበራዊ ፍትህ አንድ ብያኔ እንስጥ:: ማኅበራዊ ፍትህ ማለት በግለሰብ እና በማኅበረሰብ መካከል የሚኖርን የግዴታዎችን እና የመብቶች ተቃርኖ ለማለዘብ የሚበጅ የሚገነባ ማኅበራዊ ውል ነው:: በማኅበረሰብ እና በመንግሥት መሀል የሚኖረውን ማኅበራዊ ውል በማኅበራዊ ፍትህ ኃልዮት በኩል ስትመለከተው፣ ቅጥ ያጣ ከፍተኛ የኢኮኖሚ መደብም ሆነ የሚዘገንን ድህነት እንዳይኖር ያንን ማረቂያ ሥርዓት ነው::

የሚሆን አንድ ማሳያ ሊሆን ይችላል:: ሲገባኝ ፓርቲው ለተገፉት ማኅበራዊ ፍትህ እሰጣለሁ ሲል እነዛ ግፉዓን ወይ በሀይማኖት፣ ወይ በአካባቢ፣ ወይ በዘውግ፣ በፆታ እና በእድሜ መሰል የሥነ-ሕዝብ ተለዋጮች እንደመሆኑ ማዕከሉ ግለሰብ መሆኑን መረዳት ይቻላል:: ይቃረናል የሚሉ ሰዎች ግለሰብ የሚለውን ከግለሰብኝነት (Individual vs Individual-ism) ጋር አምታተው እየተረዱት ነው::

*ኢዜማ ከልሂቁ ውጪ የሌላውን ማኅበረሰብ ክፍል የሚማርክ ፓርቲ አይደለም በሚል አስተያየታቸውን የሚሰጡ አካላት አሉ:: በዚህ ትስማማለህ?*

እስከሆነ ልክ ድረስ እስማማለሁ:: ለሴራ ትንታኔ ብዙ ዋጋ በሚሰጥ የፖለቲካ ባህል ውስጥ በሚፈጠሩ ማኅበራዊ ሁነቶች ላይ አስተያየቱን ከመስጠት በብዛት ፓርቲው እንደመቆጠቡ፤ ወቀሳው በሆነ ልክ ትክክል ነው:: ከሌላ ጫፍ በኩል የኢትዮጵያ ፖለቲካ አንዱ ችግሩ ልሂቅነት እንደመሆኑ፤ ፓርቲው አልፎ ሂያጅ ብሎ ባመነባቸው የፖለቲካ መረባበሾች ላይ አቋሙን ከመናገር መቆጠቡን ስትደምርበት ልሂቃዊ ድርጅት ነው ብሎ የሚቀርብበትን ክስ ያጠናከረበት ይመስለኛል:: ፓርቲውንም እየጎዳው ያለም ይመስለኛል:: አንዳንዶቹን የፓርቲው ሰዎች በቲንክ ታንክ እና በፖለቲካ ፓርቲ ያውም የኢትዮጵያ የሆነ የፖለቲካ ፓርቲ መካከል ልዩነት እንዳለ እንድናስታውሳቸው ሳይገፉን አልቀሩም:: የኖርንበትን የሕዝበኝነት ፖለቲካዊ ጥቅም እንደው ባይዘነጉት መልካም ነው::

*ብልፅግና እና ኢዜማን አንድ አድርጎ የማየቱ ነገር አለ:: አንዳንዶች እንደውም ነገሩን ለጥጠውት ኢዜማ የብልፅግና ‹‹ተለጣፊ›› ነው ይሉታል:: በዚህ ላይ ምን ሀሳብ አለህ?*

በእርግጠኝነት ብርሀኑ ነጋ (ፕሮፌሰር) ከዚያች አንድ ወንበር በታች የትኛውን ስልጣን ለማግኘት ይለጠፋል ብለህ ልትቃዥ ትችላለህ? ይሄ አስተያየት ራሱ ከላይ እንደጠቀስኩልህ የፓርቲው ልሂቃዊ አካሄድ ያመጣውም ይመስለኛል::

*እኔ ማንሳት ሲኖርብኝ ያላነሳሁት ነጥብ ካለ?*

ይህን ያህል ካደረከኝ አይበቃህም::

# ኢዜማ፣ በደብረ ዘይት ከተማ ባለ የምርጫ ወረዳው ላይ ሥራውን እንዳይከውን እንቅፋት እየገጠመው እንዳለ ገለጸ

## በከተማው እስካሁን ድረስ ቢሮ ሊከፍት አልቻለም

ጥር 27 ቀን 2013 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)

የደብረ ዘይት ከተማ አስተዳደር እና ፖሊስ በኢዜማ አባላት ላይ ከፍተኛ የሆነ ጫና እያሳደረ ስለሚገኝ የድርጅት ሥራዎችን ለማካሄድ እንቅፋት እንደሆነባቸው፤ በደብረ ዘይት ከተማ የአደአ ምርጫ ወረዳ ጣቢያ አስተባባሪ ተስፋዬ ኢቲቻ ለዜጎች መድረክ ተናገሩ፡፡

የምርጫ ወረዳው አስተባባሪ፤ ባሳለፍነው ዓመት መጋቢት 2012 ዓ.ም ፖሊስ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ለማሳየት ፍቃደኛ ሳይሆን በመቅረት በቤታቸው ላይ ብርበራ እንዳካሄደ እና ከእነ ወንድማቸው በቁጥጥር ሥር እንዳዋላቸው አስታውሰዋል፡፡ በወቅቱ ድብደባ እንደደረሰባቸውም ገልጸዋል ፡፡ ከማዕከል ካሉ ኃላፊዎች ጋር ንግግር ከተደረገ በኋላም ከእስር ሊለቀቁ እንደቻሉ አስረድተዋል፡፡

በምርጫ ወረዳቸውም ሆነ በግል እሳቸው ላይ የሚደርሰው ጫና ዘንድሮም መቀጠሉን የተናገሩት ተስፋዬ ኢቲቻ፣ ጥር 21 ቀን 2013 ዓ.ም የታጠቁ 8 ፖሊሶች በመኖሪያ ቤታቸው ከጠዋቱ 2፡30 ላይ መጥተው በመኖሪያ ቤታቸው ብርበራ አካሄደው በኦሮምኛ እና በአማርኛ ኢዜማ ያዘጋጃቸው የተለያዩ ሰነዶች፣ መጽሐፍት፣ ከአባላት ገንዘብ የሚሰበሰብበት የገንዘብ ደረሰኝ፣ የአባልነት መመዝገቢያ ቅፅ እና ስቲከሮች እንደተወሰደባቸው ለዜጎች መድረክ ገልጸዋል፡፡ እነዚህ ሕጋዊ የፓርቲው ሰነዶች እንዲመለሱ፤ ይህ ዜና እስከተጠናቀረበት ጥር 26 ቀን 2013 ዓ.ም ድረስ ለፖሊስ ተደጋጋሚ ጥያቄ ቢያቀርቡም ምንም ዓይነት ምላሽ እንዳላገኙ ለዝግጅት ክፍላችን አስታውቀዋል ፡፡

የከተማውን ፖሊስ መምሪያ ኃላፊ በስልክ ቢያነጋግሩም፣ በአካል ቀርባችሁ እንነጋገር እንደተባሉ እና በአካል ቀርበው ለመነጋገር ግን ሕጋዊና ምክኒያታዊ መሰረት ካላችሁ፤ መጥሪያ ልትልኩልን ይገባል የሚል ምላሽ ለከተማው ፖሊስ መምሪያ ኃላፊ መስጠታቸውን የምርጫ ወረዳው አስተባባሪው ጠቁመዋል፡፡ መጥሪያ እስከቀረበላቸው ድረስም በአካል ቀርበው ለመነጋገር ችግር እንደሌለባቸው ተናግረዋል፡፡ ይህ ዜና እስከተጠናቀረበት ጥር 26 ቀን 2013 ዓ.ም ድረስም ምንም ዓይነት መጥሪያ እንዳልደረሳቸው አስረድተዋል፡፡

ከአባላትና ከደጋፊዎቻቸው ጋር ሕዝባዊ ስብሰባ ለማድረግ ለከተማው አስተዳደር አሳውቀው እንቅስቃሴ ሲጀምሩ የተለያዩ እንቅፋቶች እየገጠሟቸው እንዳሉ የገለፁት የምርጫ ወረዳው አስተባባሪ ተስፋዬ ኢቲቻ፣ ሕዝባዊ ስብሰባውን ማካሄድ እንደማይችሉ ከከተማው አስተዳደር በኩል የሚገለፅላቸው ምክኒያት ምን እንደሆነ ላነሳንላቸው ጥያቄ ሲመልሱ ‹‹ኦነግ ሸኔና አባ ቶርቤ በደብረ ዘይት ከተማ ስለገቡ ሊገድሏችሁ ይችላሉ፤ አራዝሙት›› የሚል ምላሽ ሲሰጣቸው እንደቆየ ተናግረዋል፡፡ በከተማው ውስጥ እስካሁን ድረስ ቢሮ ሊከፍቱ እንዳልቻሉና ከአባሎቻቸው ጋርም በራሳቸው መኖሪያ ቤት እንደሚሰበሰቡ የጠቆሙት የምርጫ ወረዳው አስተባባሪ፣ ቢሮ ለመከራየት ከሕንፃ አከራዮች ጋር ስምምነት ከፈጸሙ በኋላ ውል ሊገቡ ሲሉ አከራዮቹ ሀሳባቸውን ቀይረው ቢሮ ለማከራየት ፍቃደኛ እንዳልሆኑ እየገለፁላቸው እንደሚገኝ ጠቁመዋል፡፡ ይህም እየሆነ ያለው የመንግሥት አካላት በአከራዮቹ ላይ ጫና እያሳደሩ ስለሚገኝ መሆኑን የምርጫ ወረዳ አስተባባሪው ተናግረዋል፡፡

በደብረ ዘይት የገጠማቸውን ችግር በውይይት ለመፍታት ከተማው ድረስ በመሄድ ሙከራ ማድረጋቸውን ለዜጎች መድረክ የገለጹት የኢዜማ ዋና ጸሀፊ አበበ አካሉ፣ ወደ ደብረ ዘይት ባቀኑበት ጊዜ ከብልፅግና ጽህፈት ቤት ኃላፊና የፖለቲካ ዘርፍ ተጠሪ ጋር ውይይት ማካሄዳቸውን ነግረውናል፡፡ ኢዜማ በከተማው ቢሮ የመክፈት መብት እንዳለውና ይህንን አምነው ሊቀበሉ እንደሚገባ እንደነገሯቸው ገልፀዋል፡፡ ኦነግ ሸኔ እና አባ ቶርቤ አካባቢው ላይ ያስቸግረናል የሚል ምላሽ እንደሰጧቸው፤ ይህንን የመጠበቅና ፀጥታ የማስከበር ኃላፊነት የመንግሥት መሆኑን እንደነገሯቸው የተናገሩት ዋና ፀሀፊው፣ ከአዲስ አበባ 42 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በሚገኝ ከተማ ኦነግ ሸኔ ያስቸግረናል ስትሉ ልታፍሩ ይገባል የሚል ምላሽ እንደሰጧቸው ተናግረዋል፡፡ ‹‹ኢዜማ ደብረ ዘይት ቢሮ ሲከፍት ነው ወይ ኦነግ ሸኔ የሚበጠብጠው?›› ሲሉ ጥያቄ ማቅረባቸውን የጠቆሙት ዋና ፀሀፊው፣ ረቡዕ ጥር 26 ቀን 2013 ዓ.ም ለዐቢይ አህመድ የድጋፍ ሰልፍ በደብረ ዘይት ከተማ መካሄዱን ጠቅሰው ‹‹ለእነሱ የድጋፍ ሰልፍ ሲሆን ኦነግ ሸኔ አያስቸግርም፤ እኛ ስንንቀሳቀስ ግን ኦነግ ሸኔ ያስቸግራል፡፡ እነሱ ያንን ሁሉ ሰው ለድጋፍ ሰልፍ ይዘው ሲወጡ ኦነግ ሸኔ ለምን አያስቸግራቸውም? እኛ መቶ ሰው ለመሰብሰብ ኦነግ ሸኔ ያስቸግራችኋል እንባላለን፡፡ እነሱ የድጋፍ ሰልፍ ሲወጡ ግን ኦነግ ሸኔ አያስቸግርም›› በማለት በመንግሥት አካላት በኩል እየቀረበ ያለው ምክነያት ተቀባይት የሌለው መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ከደብረ ዘይት በተጨማሪ በምስራቅ ሸዋ ላይ የፓርቲያቸውን እንቅስቃሴ የመገደብ ፍላጎት እንዳለ የገለፁት ዋና ፀሀፊው አበበ አካሉ፣ ይህም እየሆነ ያለው ኦሮሚያ ላይ ፓርቲያቸው ካለው ጠንካራ መዋቅር አንዱ ምስራቅ ሸዋ ስለሆነ መሆኑን ተናግረዋል፡፡ ‹‹እያየናቸው ያሉት ምልክቶች እንፈልገዋለን ከምንለው ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መስፈንና ፍትሀዊ ምርጫ ከማካሄድ አንፃር የሚሄዱ ባለመሆናቸው ሊቆሙ የሚገቡ ናቸው›› ሲሉ ለዜጎች መድረክ የተናገሩት የኢዜማ ድርጅት ጉዳይ ኃላፊ ዋሲሁን ተስፋዬ፣ በደብረ ዘይት፣ በዳውሮ እና በአላባ በአባሎቻቸው ላይ እየደረሰ የሚገኘውን ጫና አጥብቀው እንደሚያወግዙ ተናግረዋል፡፡ ‹‹ይህን መሰሉ ድርጊትም እንዲታረም›› ሲሉ ጠይቀዋል፡፡ ይህንን ድርጊት ልንታገስ አንችልም ያሉት ድርጅት ጉዳይ ኃላፊው፣ ይህንን ጥፋት ያጠፉ የመንግሥት አካላት በሕግ አግባብ መጠየቅ አለባቸው ብለዋል፡፡ በደብረ ዘይት ከተፈጠረው ችግር ጋር በተገናኘም ከከተማዋ ከንቲባ ጋር ለመነጋገር ቀጠሮ መያዛቸውን ተናግረዋል፡፡





# ‹‹የኮንሶ ሕዝብ የመንግሥትም የሚዲያም ትኩረት ተነፍጎታል››

አበበ አካሉ (የኢዜማ ዋና ጸሐፊ)

ጥር 27 ቀን 2013 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)



የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) በተለያዩ የአገሪቱ ቦታዎች የተፈጠረውን ቀውስ የሚያጠና ግብረ ኃይል ወደ ትግራይ፣ መተከል፣ ማይካድራ እንዲሁም ኮንሶ በማሰማራት መረጃዎችን በመሰብሰብ ለሕዝቡ ይፋ ለማድረግ እየሰራ እንደሚገኝ ይታወቃል፡፡ ግጭት ከተፈጠረባቸው እና መረጃዎች እንዲሰበሰብ ከተወሰነባቸው ቦታዎች መካከል ኮንሶ አንዱ ሲሆን፤ በኮንሶ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ተመልከተው እንደመጡ የኢዜማ ዋና ጸሐፊ አበበ አካሉ ለዜጎች መድረክ ገልጸዋል፡፡

በኮንሶ በተፈጠረ ግጭት ምክነያት ከአንድ መቶ ሺ በላይ ዜጎች ከኅዳር 8 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለው በትምህርት ቤቶች እና በሜዳ ላይ እያደሩ እንደሚገኙ፤ የቤት እንስሳቶቻቸው እንደተዘረፉ፤ ሰብሎቻቸውም መቃጠላቸውን እና አሁንም ድረስ ተፈናቃዮቹ ወደ ቤት ንብረታቸው መመለስ እንዳልተቻለ ያስረዱት ዋና ጸሐፊው፣ ቀይ መስቀል እና ሴቭ ዘ ችልድረን ለተፈናቃዮች በቂ በሚባል ደረጃ ባይሆንም የተወሰነ ድጋፍ እያደረጉ እንደሚገኝ ጠቅሰዋል፡፡

‹‹የኮንሶ ሕዝብ የመንግሥትም የሚዲያም ትኩረት ተነፍጎታል›› ያሉት ዋና ፀሀፊው፣ ከአንድ ወር በኋላ ዝናብ መጣል የሚጀምርበት ወቅት እንደመሆኑ መጠን፤ ሕዝቡ ወደነበረበት ካልተመለሰ በዝናብ ወቅት ምርት ማምረት ስለማይችል በቀጣዩ ጊዜያት ለከፍተኛ ችግር ሊጋለጥ እንደሚችል ጠቅሰዋል፡፡ በቂ መጠለያ ባለመኖሩ የተነሳም ህጻናትና አዛውንቶች ለከፍተኛ ችግር ስለሚጋለጡ ተገቢውን ትኩረት ለኮንሶ ሕዝብ መስጠት እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡ መንግሥት ለኮንሶ ሕዝብ ትኩረት እንዲሰጠው ጫና ከማድረግ ባለፈ ጉዳዩን ለዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ በማሳወቅ ተፈናቃዮቹ ድጋፍ እንዲያገኙ የማድረግ ሥራ እንደሚሰሩ አሳውቀዋል፡፡

ኢዜማ ቀውስ ወደ ተከሰተባቸው አካባቢዎች የላካቸው ልዑካን፣ ሥራቸውን አጠናቀው ሲመለሱ በሥራ አስፈጻሚ ደረጃ ውይይት ተደርጎበት፤ ልዑክ ቡድኑ የደረሰበትን ዝርዝር ጥናት ለሕዝብ በሪፖርት መልክ ይፋ የሚያደርግ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡



በከንባታ ጠንባሮ ዞን አንጋጫ ምርጫ ወረዳ ሊቀመንበር የነበሩት ሳዱሬ ተክሌ፣ ባጋጠማቸው ድንገተኛ የመኪና አደጋ ሕይወታቸው ሊያልፍ ችሏል፡፡ ሳዱሬ ተክሌ፣ የኢዜማ መሥራች አባል ሲሆኑ ሕይወታቸው እስካለፈበት ቀን ድረስም ጊዜያቸውን፣ ገንዘባቸውን እንዲሁም ጉልበታቸውን ሳይሰስቱ ለኢዜማ ሲያበረክቱ የነበሩ ጠንካራ አባል ነበሩ፡፡ ከኢዜማ በተጨማሪም አርበኞች ግንቦት ሰባት ውስጥ ከፍተኛ ተሳትፎ ሲያደርጉ የነበሩ ነባር ታጋይ ሲሆኑ፣ አርበኞች ግንቦት ሰባት ከከሰመ በኋላ ኢዜማን በመቀላቀልና በስደት ይኖሩበት ከነበረው ደቡብ አፍሪካ በመመለስ፤ ትውልድ ቦታቸው ወደ ሆነው ከንባታ ጠንባሮ ዞን በማምራት የአንጋጫ ምርጫ ወረዳን በማቋቋም ሲሠሩ ነበር፡፡ ሕይወታቸው እስካለፈበት ቀን ድረስም የምርጫ ወረዳውን በሊቀመንበርነት መርተዋል፡፡

ኢዜማ በመላው የድርጅታችን አባላት ስም በሳዱሬ ተክሌ ህልፈተ ህይወት የተሰማውን ጥልቅ ሀዘን ይገልጻል፡፡ ለቤተሰቦቻቸው፣ ለወዳጆቻቸው እና ለትግል አጋሮቻቸው መጽናናትን ይመኛል፡፡

# የታዛቢዎች ምልመላ ሥራ በተጠናከረ ሁኔታ መሠራት እንዳለበት ተገለጸ

ጥር 27 ቀን 2013 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ድርጅት ጉዳይ ኃላፊ ዋሲሁን ተስፋዬ፣ ምርጫ ወረዳዎችና ዕጩዎች ታዛቢዎችን መለየትና መመልመል ሥራ ላይ ዝግጁ ሊሆኑ እንደሚገባ አሳሰቡ፡፡

«ያለ ታዛቢ የሚደረግ ምርጫ ምንም ትርጉም የሌለው ምርጫ ነው» ያሉት ዋሲሁን ተስፋዬ፣ ምርጫን ከማሸነፍ አንጻር የታዛቢ ምልመላ ቁልፍ ፋይዳ እንዳለው ጠቁመዋል፡፡ ኃላፊነቱም በዋናነት የምርጫ ወረዳዎቹ ሥራ ነው ያሉት ድርጅት ጉዳይ ኃላፊው፣ ከምርጫ ወረዳዎቹም የዕጩዎቹ ኃላፊነት ድርሻ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ በምርጫ ወረዳው በሚገኙ ጣቢያ ልክ ሁለት ሁለት ታዛቢዎችን መመልመልን አቅደው እየሰሩ እንደሚገኙ የጠቀሱት ኃላፊው፣ ታዛቢ የማያስቀምጡበት አንድም የምርጫ ጣቢያ እንደማይኖር ጠቁመዋል፡፡ ተንቀሳቃሽም ሆነ ቋሚ ታዛቢዎች በየምርጫ ወረዳው እናስቀምጣለን ሲሉ ተናግረዋል፡፡

የፓርቲያቸው መዋቅር ይህንን ሥራ አስቀድሞ ሲሰራበት እንደቆየ ያስታወሱት ኃላፊው፤ ከኮቪድ ወረርሽኝ ጋር በተያያዘ የምርጫ ጣቢያዎች ቁጥር እንዲጨመር መደረጉን ተከትሎ፣ ከዚህ በፊት ከነበሩ ምርጫዎች በተለየ ሁኔታ በርካታ ታዛቢ እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል፡፡ ለዚህም ሲባል የታዛቢ ምልመላ ሥራ በተጠናከረ ሁኔታ መሠራት እንዳለበት የተናገሩት ኃላፊው፣ በሚቀጥሉት ጥቂት ጊዜያት ውስጥ ምርጫ ወረዳዎችና ኢዜማን ወክለው በየምርጫ ወረዳው የሚወዳደሩ ዕጩዎች፣ የታዛቢ ምልመላ ሥራን በሚገባ ሊከውኑት ይገባል ብለዋል፡፡
ታዛቢዎቹ ከተመለመሉ በኋላ ታዛቢዎቹ ምን ይሠራሉ? የሥራ ድርሻቸውስ ምን ሊሆን ይገባል? በሚሉ ነጥቦች ላይ ሰነድ እየተዘጋጀ ያለ ሲሆን የሰነዱ ዝግጅት ከተጠናቀቀ በኋላ ለታዛቢዎቹ የሚሆን በቂ ስልጠና የሚሰጥ ይሆናል፡፡

የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ እና የምርጫ ሥነ-ምግባር አዋጅ 1162/2011 ማንኛውም ለምርጫ ዕጩ ያቀረበ የፖለቲካ ፓርቲ የምርጫውን ሂደት የሚከታተሉ በእያንዳንዱ የምርጫ ጣቢያ እየተቀያየሩ የሚሰሩ ሁለት ተቀማጭ ወኪሎችን መሰየም እንደሚችል ይደነግጋል፡፡

# የኢዜማ ምርጫ ወረዳ 25 ሕዝባዊ ስብሰባ አደረገ

ጥር 27 ቀን 2013 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ከምርጫ ወረዳ 25 አባላትና ደጋፊዎች ጋር ጥር 23 ቀን 2013 ዓ.ም በኮልፌ ገነት ሲኒማ አዳራሽ በማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች እንዲሁም በኢዜማ የሙያ ማኅበር ፖሊሲ ዙሪያ ውይይት አደረገ፡፡

ኢዜማ በምርጫ ወረዳው 25 ውስጥ የሚገኙ አባላቱን በማቀናጀት ሕብረተሰቡን የማንቃት፣ የዜግነት ፖለቲካ ግንዛቤ የማስጨበጥ፣ ፓርቲውን የማስተዋወቅ፣ ገቢ የማሰባሰብ እና አዳዲስ አባላትን የመመዝገብ እንቅስቃሴ በሚያደርግበት ወቅት ሕብረተሰቡን የማወያየት ችግራቸውንም የመስማት እንዲሁም በፓርቲው ላይ ያላቸውን ተስፋ እና ስጋት የማወቅ እድል በማግኘቱ ለሕብረተሰቡ ምላሽ ለመስጠት የፓርቲው አመራሮች ብርሃኑ ነጋ (ፕ/ር)፣ ከውሰር እንድሪስ እና ኑሪ ሙደሲር በመጋበዝ ከውይይቱ ተሳታፊዎች ለተነሱት ጥያቄዎች ምላሽ እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡

የኢዜማ መሪ ብርሀኑ ነጋ (ፕሮፌሰር) ከተሳታፊዎች ፓርቲውን በተመለከተ ለተነሳላቸው ጥያቄዎች ጠቅለል ባለ መልኩ «ውሸት ሲደጋገም እውነት ይሆናል፡፡ ለሀሰተኛ መረጃዎች ጊዜ መስጠት የለብንም፡፡ የመረጃ ምንጫችንን መለየት፣ መረጃን ባገኘን ጊዜ ቢያንስ የተወሰነ ርቀት ሄደን የመረጃውን እውነትነት ማጣራት ይገባል» ያሉ ሲሆን ሃይማኖት ተኮር ለሆኑ ጥያቄዎችም ሲመልሱ በግላቸው ለዕምነቶች ተገቢውን ክብር እንደሚሰጡ በመግለጽ፣ ሁሉም ዕምነቶች ማኅበረሰብን በሥነ-ምግባር የማነጽ፤ ሕዝቡን የማረጋጋት፤ አማኙ ከሌላ ማኅበረሰብ ጋር ተቀራርቦ ተግባብቶ እንዲኖር የሚያስተምሩ ናቸው ብለዋል፡፡

በዕለቱ የምርጫ ወረዳ 24 እና 25 ዕጩ ተወዳዳሪዎች በውይይቱ ለተገኙት ተሳታፊዎች የአጭር ደቂቃ ንግግር በማድረግ ራሳቸውን አስተዋውቀዋል፡፡ በ2013 ዓ.ም በሚደረገው ሀገር አቀፍ ምርጫ ላይ ከምርጫ ወረዳ 24 ጋር በመተጋገዝ በምርጫ ቅስቀሳ ወቅት አብሮ በመሥራት ምርጫውን በአሸናፊነት ለመወጣት በጋራ እንደሚሰሩ ገልጸዋል፡፡
በዕለቱ የገቢ ማሰባሰብ እና አዳዲስ አባላት የመመዝገብ ሥራ መሥራት መቻላቸውን የምርጫ ወረዳ 25 ሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አርአያ ሥላሴ ቦጋለ ለዜጎች መድረክ ገልጸዋል፡፡





# ኢዜማ በ406 ምርጫ ወረዳዎች ላይ ዕጩዎቹን አስመረጠ

ጥር 27 ቀን 2013 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)



የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ከጥር 01 ቀን እስከ ጥር 23 ቀን 2013 ዓ.ም ድረስ ባወጣው የዕጩዎች የምርጫ ጊዜ ሰሌዳ መሠረት በ406 ምርጫ ወረዳዎች ላይ የእጩዎች ምርጫ አድርጎ ማጠናቀቁን የኢዜማ ድርጅት ጉዳይ ኃላፊ ዋሲሁን ተስፋዬ ለዜጎች መድረክ ገለጹ፡፡

ኢዜማ ባወጣው የሶስት ሳምንት የጊዜ ሰሌዳ በደቡብ ክልል 123 ወረዳዎች፣ በአማራ ክልል 135 በኦሮሚያ ክልል ከ100 በላይ ምርጫ ወረዳዎች፣ በአዲስ አበባ፣ በሐረሪ፣ በጋምቤላ፣ አፋር ሙሉ በሙሉ፣ በሱማሌ፣ በቤንሻንጉል ጉምዝ ደግሞ ከተወሰኑ ቦታዎች ውጭ የዕጩዎች ምርጫ ማደረጉን ኃላፊው አስረድተዋል፡፡ በቀጣይ ጊዜያት በቀሩት ምርጫ ወረዳዎች ምርጫውን በማድረግ እንደሚያጠናቅቁ ዋሲሁን ተስፋዬ የገለጹ ሲሆን፤ በተወሰኑ ምርጫ ወረዳዎች ላይ የዕጩዎችን ምርጫ ማካሄድ ያልቻሉት በጸጥታ ችግር እና በአዳራሽ እጦት ምክንያት የተነሳ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ዕጩዎቹ በምርጫው ላይ ቅሬታ ቢኖራቸው ቅሬታው የሚፈታው በምን ዓይነት መልኩ ነው? ብላ የዜጎች መድረክ ለጠየቀቻቸው ጥያቄ ኃላፊው፣ ማንኛውም አካል በምርጫው ላይ ቅሬታ ካለው በሶስት ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ወረዳው ላይ ላለ ለዲሲፕሊን ኮሚቴ ማቅረብ ይችላል ብለዋል፡፡ የወረዳው ዲሲፕሊን ኮሚቴ ለቅሬታው አጥጋቢ ምላሽ ካልሰጠ ደግሞ ለብሔራዊ ዲሲፕሊን ኮሚቴ ቅሬታውን ማቅረብ እንደሚችል ጠቁመዋል፡፡

በተካሄደው የዕጩዎች ምርጫ እየቀረቡ ያሉት ቅሬታዎች ጥቂት ሲሆኑ፤ በወረዳ እና በብሔራዊ ደረጃ በሚገኙ ዲሲፕሊን ኮሚቴዎች ውሳኔ የተሰጠባቸው መኖራቸውን ኃላፊው ገልጸዋል፡፡ አርባ ምንጭ እና ወልቂጤ ከተማዎች ላይ የቀረበውን ቅሬታ ተከትሎም ምርጫው መደገሙን አሳውቀዋል፡፡

ኢዜማ በትግራይ፣ ምስራቅና በምዕራብ ወለጋ እንዲሁም አንዳንድ ቦታዎች ባለው የጸጥታ ችግር ምክንያት አባላትን መልምሎ ምርጫ ለመወዳደር እንዳልቻለ በመግለጽ ዕጩዎች ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ባስቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ከየካቲት 08 እስከ 21 ቀን 2013 ዓ.ም ድረስ በምርጫ ወረዳቸው ላይ መመዝገብ እንደሚገባቸው፣ ዕጩዎቹ ዘመቻውን የሚመሩት ራሳቸው በመሆናቸው ዘመቻውን እንዴት ማካሄድ እንዳለባቸው የሚያሳውቅ ሥልጠና ለመስጠት ዝግጅት እያደረገ ይገኛል፡፡

# የኢዜማ የሙያ ማኅበራት፣ ባዘጋጀው ፖሊሲ ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት አደረገ

ጥር 27 ቀን 2013 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)







የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ጥር 23 ቀን 2013 ዓ.ም በኢዜማ የሙያ ማኅበራት ፖሊሲ ላይ በአገሪቱ ውስጥ ከሚገኙ ሙያ ማኅበራት ጋር በእምቢልታ ሆቴል ውይይት አደረገ፡፡

ኢዜማ ሙያ ማኅበርን በሥራ አስፈጻሚ ደረጃ በማዋቀር በኢትዮጵያ የመጀመሪያ ፓርቲ ሲሆን በሙያ ማኅበራት ዘርፍ ያዘጋጀውን ፖሊሲ የኢሰማኮ ፌዴሬሽኖች፣ የኢትዮጵያ መምህራን ማኅበር ፌዴሬሽን፣ የኢትዮጵያ መምህራን ማኅበር፣ ያልተደራጁ የግል ትምህርት ቤቶች መምህራን፣ የሠራተኞች ማኅበር እና ሌሎችም የሙያ ማኅበራት በተገኙበት ፖሊሲውን በማቅረብ በረቂቁ ላይ በመወያየት ከተጋባዥ እንግዶች የተለያዩ ግብዓቶች ማግኘታቸውን የኢዜማ ሙያ ማኅበር ቋሚ ኮሚቴ ለዜጎች መድረክ አሳውቋል፡፡

ኢዜማ ባዘጋጀው የፖሊሲ ውይይት ላይ የሙያ ማኅበራቶቹ ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት ተወካዮችን የላኩ ሲሆን፤ የኢዜማ መሪ ብርሃኑ ነጋ (ፕሮፌሰር) እና የኢዜማ የፖሊሲ አስተባባሪ አማን ይኹን ረዳ በውይይቱ ላይ ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ በውይይቱ ተሳታፊ የሆኑት የሙያ ማኅበራት ከኢዜማ ጋር በጋራ ለመሥራት ፍቃደኛ መሆናቸው ገልጸዋል፡፡

ኢዜማ የኢትየጵያን የሥራ ባህል በመፈተሽ ጉድለቶችን በማየት፣ በመገናኛ ብዙኃን ጭምር ስለ ሥራ ባህል የማስተማር ሥራ ለመስራት እንዳቀደ፣ ሠራተኛው ራሱን እና ቤተሰቡን ማስተዳደር በማይችልበት ደረጃ ላይ በመገኘቱ ይሄን ለመቅረፍ ከማኅበራቱ ጋር ተባብሮ በመሥራት፤ የሠራተኞችን ህይወት ለመቀየር እንደሚጥር ለሠራተኞች እና ለድርጅቶች ሙያዊ ሥልጠና የመስጠት እቅድ እንዳለው በመድረኩ ላይ ገልጿል፡፡

የኢዜማ ሃሳቦች በሠራተኞች ቅቡልነት እንዲኖረው ለማድረግ፣ ተቋማቱ ለሠራተኞች ሰላም የሰፈነበት ከባቢ የሥራ ሁኔታ እንዲፈጠር፣ ሠራተኞች በሚሰሩት ሥራ ላይ በሚያገኟቸው ነገሮች ላይ የመደራደር እና መብቶቹን የማስከበር አቅም እንዲኖራቸው፣ ለሕጻናት የሥራ ክቡርነት የሚያሳይ የማስተማር ሥራዎች ላይ ትኩረት በመስጠት እንደሚሰራ ከሙያ ማኅበራት ቋሚ ኮሚቴ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡


## የኢዜማ ዋና ጽሕፈት ቤት አድራሻ

ስታዲየም፣ ራስ ደስታ ዳምጠው መንገድ

አዲስ አበባ

+251115258025/26

www.ethzema.org

Secretariat@ethzema.org